# ነፍሰጡር ሰራተኞች እና አዲስ ወላጆች

## እርግዝና በ ሥራ ላይ

ነፍሰጡር ከሆኑ የሐኪም ማስታወሻ ሳያቀርቡ የሚከተሉትን ጥቅሞች የመጠየቅ መብት አልዎት። አሠሪዎ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት:-

- ተደጋጋሚ እና ረጂም የመጸዳጃ ቤት፣ የምግብ እና የውሃ ዕረፍቶች:-
- ወንበር፣ እና
- ከ20 ፓውንድ በላይ ለማንሳት የተቀመጡ ገደቦች።

ሌላ የሥራ ቦታ የመጠየቅ መብት አልዎት
ከሚከተለው አካል ምክር ሲሰጡ የሚደረጉ ለውጦችከ
ከጤና ክብካቤ አቅራቢ ወይም ከአዋላጅ። አሠሪዎ የሥራ ቦታዎ ሁኔታዎች እንዲያስተካክሉ መጠየቅ አይችልም
እርስዎ ነፍሰጡርስለሆኑ

## የእርግዝና እና የወላጅነት ዕረፍት ከሥራ

Minnesota's Paid Leave program ለአብዛኞቹ ሰራተኞች በእርግዝና ወቅት፣ ልጅ ከመውለድ በኋላ ወይም ከልጁ ጋር ለመቀራረብ የሚከፈልበት የዕረፍት ሰዓት እና የሥራ ጥበቃ ያቀርባል።

ለሚከተሉት የሚከፈልበት ዕረፍት ሊወስዱ ይችላሉ ለ:-

- ከእርግዝና ጋር የተያያዙ የጤና ፍላጎቶች:-
- ልጅ መውለድ እና ማገገም:-
- እንደ የሚወልድ ወይም የማይወልድ ወላጅ የሚሰጥ የመቀራረቢያ ጊዜ፣ እና
- ከጉዲፈቻ ወይም ከሞግዚትነት ምደባ በኋላ መቀራረብ።

ብቁ ከሆኑ፣ ለእራስዎ ክብካቤ እስከ 12 ሳምንታት እንዲሁም 12 ሳምንታት ለመቀራረብ፣ በጣምራ ድምር እስከ 20 ሳምንታት መውሰድ ይችሉሉ። የመቀራረብ ዕረፍት ልጁ ከተወለደበት፣ ከጉዲፈቻ ወይም ከሞግዚትነት ምደባ ጀምሮ ባሉ 12 ወራት ውስጥ መጠቀም ይገባል። በሚከፈልበት ዕረፍት ላይ ሳሉ፣ የመደበኛው ክፍያዎ ክፍልከመንግሥት ይቀበላሉ።

የሚከፈልበት ዕረፍት ከፌዴራል የቤተሰብ እና የሕክምና ዕረፍት ሕግ (FMLA) ጥበቃዎች ጋር ሊደረብ ይችላል። ለሚከፈልበት ዕረፍት ወይም FMLA ብቁ ካልሆኑ የሚኒሶታ ሕግ አሁንም 12 ሳምንታት በሥራ የተጠበቀ የማይከፈልበት የወላጅነት ዕረፍ ያቀርባል። ይህ ዕረፍት የስደት ሁኔታዎ ምን ይሁን ምን፣ ለስንት ያክል ጊዜ ለአሰሪዎ እንደሰሩ ወይም የአሠሪዎ መጠን ምን ይሁን ምን ማግኘት ይቻላል።

ስለ ብቁነት፣ እንዴት ማመልከት
እንደሚችሉ እና የአሰሪዎ
መስፈርቶች በ
spaidleave.mn.gov.ላይ
ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።



## በ ሥራ ላይ ወተት መጭመቅ

በሥራ ላይ ወተት ለመጭመቅ ከወሰኑ
አሠሪዎ፣
መጠን ምን ይሁን ምን፣ የሚከተሉትን ማቅረብ
አለበት:-

- ክፍያዎን ሳያጡ ወተት የሚጨምቁባቸው የዕረፍት ጊዜያት፣ እና
- ንፁህ፣ የግል እና ድሕንነቱ የተጠበቀ ቦታ ወተት ለመጭመቅ ይህም:-
  - መታጠቢያ ቤት ያልሆነ:-
  - ከ እይታ የተከለለ:-
  - ከሥራ ባልደረቦች እና ከህዝብ ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነ፣
  - ከሥራ ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ፣ እና
  - የኤሌክትሪክ ሶኬት ማግኘት የሚቻልበት።

በዚህ መስፈርት ላይ ውስን ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

በፍላጎትዎ መሠረት፣ ይህ ማለት አሁን ላይ ባለ የሚከፈልበት ዕረፍት ወይም እንደ የአእምሮ ዕረፍት ያለ አሁን ላይ ባለ የማይከፈልበት ዕረፍት ወይም በሌላ ጊዜ ወተት የሚጨምቁበት ጊዜ መምረጥ ይችላሉ።

ለአሰሪዎ የበቀል እርምጃ መውሰድ ሕጉን ይጻረራል፣
ወይም ዕረፍት ለመውሰድ፣ የእርግዝና ጥቅሞች ወይም በሥራ ላይ ወተት ለመጭመቅ ዕረፍት በመጠየቅዎ በእርስዎ ላይ አሉታዊ እርምጃ መውሰድ ሕጉን ይጻረራል።

## እኛን ያነጋግሩን

Labor Standards በ651-284-5075 or
dli.laborstandards@state.mn.us. ያነጋግሩ።

DEPARTMENT OF LABOR AND INDUSTRY
Labor Standards • 443 Lafayette Road N. • St. Paul, MN 55155
651-284-5075 • dli.mn.gov • dli.laborstandards@state.mn.us

ማስታወሻ:- ይህ የሚኒሶታ ሕግ አጭር ማጠቃለያ ነው። ይህ እንደ መመሪያ የታሰበ ነው እና ተያያዥ የሚኒሶታ ሕጎችን የሚተካ ተደርጎ ኣይታሰብም።